# ቁርዓን እና የቁርዓን ህዝቦች

---

**አል ፋሩቅ**

**የቁርአን ሒፍዝ ማዕከል**

## (ጌታዬ ሆይ! ዕዉቀትንም ጨምርልኝ በል)

## ቅዱስ ቁርአን 20 : 114

بســـــم الله الرّحمن الرّحيم

ታዕምራቱ የማያልቀውንና ሀቅን ከባጢል የለየውን ታላቁን ቁርዓን ያወረደልን አላህ ምስጋና ይገባው። እንዲሁም ይህንን የአላህን መጽሃፍ ወደ እኛ በተገቢው መልኩ ባደረሱት ነብይ እና ቁርዓንን በተከተሉት ህዝቦች ላይ ሀሉ አላህ እዝነቱንና ሠላሙን እንዲያወርድባቸው እለምነዋለሁ።

በመቀጠል፡-

## ቁርዓን የዓለም ብርሀን

ቁርዓን ለሰዉ ልጆች መመሪያ ይሆን ዘንድ በመልዓኩ ጂብሪል አማካኝነት ወደ ነብዩ ሙሀመድ የተወረደ የመጨረሻዉ ኪዳን ነው። አላህ ለሰዉ ልጆች ሁሉ ብርሀን አድርጎታል። እምነትንም ይሁን ድንጋጌን ያካተተ ሲሆን ለሰዉ ልጆችን የህይወት ቀመር አስተካክሏል።

## የቁርዓን ስያሜዎች

ቁርዓን የተለያዩ ስሞች አሉት። ይህም ክብሩን እና ልቅናውን ለማመልከት ነው። ከስሞቹ መካከል፡-

1- አል-ፉርቃን

2- አል-ኪታብ

3- አል-ሁዳ

4- አል-ኑር

5- አል-ሺፋዕ

6- አል-በያን

7- አል-መውዒዟ

8- አል-ራህማ በመሳሰሉት ተጠርቷል፡፡

## ልዩ መፅሀፍ

ቁርዓንን ከቀደምት ከአላህ የተወረዱ መፅሀፍት ለየት የሚያደርጉት ብዙ ነገሮች አሉ፡፡ ለምሳሌ፡-

<u>ቁርዓን በአላህ የተጠበቀ ነው፡</u>- ሊሰረዝ ወይም ሊደለዝ ሊጨመርበትም ሆነ ሊቀነስበት አይችልም፡፡ አላህ በሰዎች ልቦና ዉስጥ በቀላሉ እንዲያዝ አድርጎታል፡፡ አላህ ይህንን በሚከተለው አንቀጽ ገልፆልናል፡-

﴿ n m l k j i h g ﴾ الحجر: ٩

‹‹እኛ ቁርዓንን እኛው አወረድነው እኛም ለርሱ ጠባቂዎቹ ነን››አል-ሒጅር 9 2. <u>በአገላለፁም ሆነ በቃላቱ ሰዎችንም ሆነ ጂኖችን ረቷል፡</u>- ቁርአንን የመሰለ ሊያመጡ አልቻሉም:: ምንም እንኳን አረቦች በግጥም እና በአርብኛ ቋንቋ አገላለፆች የረቀቁ ቢሆኑም ቁርዓንን የመሰለ ሊያመጡ አልቻሉም! ተሸንፈዋል፡፡ አላህ ይህንን ሲገልፅልን እንዲህ ይላል፡

﴿ ? > = < ; : 9 8 7 6 5 4 3 2 1 0 / . - , ﴾ الإسراء: ٨٨

<‹ሰዎችም ጋኔኖችም የዚህን ቁርዓን ብጤ በማምጣት ላይ ቢሰበሰቡ ከፊላቸው ለከፊሉ ረዳት ቢኾንም እንኳ ብጤውን አያመጡም! በላቸው›› አል-ኢስራዕ 88

3. አላህ ቁርአንን ለማስታወስ ገር አንዳደረገዉ ተናግሯል፡፡ ከሌሎች መፅሀፍት በተለየ መልኩ በቃል ይሸመደዳል፡፡

﴿ u t s r q p o n ﴾ القمر: ١٧

‹ቁርአንንም ለማስታወስ (ለመገንዘብ) በእርግጥ አገራነው፤ተገንዛቢም አለን?› አል-ቀመር17

በአለም ላይ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ከመጀመሪያዉ አስከ መጨረሻዉ በቃላቸዉ አጥንተዉታል፡፡ ከአምስት አመት እድሜ በታች ባሉ ህፃናት ሳይቀር! ይህ ታላቅነቱን የሚያሳይ ልዩ ተዓምር ነዉ፡፡

# ቁርዓንን ማንበብና መሀፈዝ (በቃል ማጥናት)

ቁርዓንን ማንበብና መሀፈዝ (መሸምደድ) ጥቅሙ ምንድን ነው? ቁርዓንን በምንቀራ ሰዓት በየአንዳንዱ ፊደል አስር አጅር (ምንዳ) እናገኛለን። ቁርዓንን ማንበብና መሃፈዝ በጣም ከፍተኛ ደረጃ የሚያስገኙ ተግባሮች ናቸው። ያላቸውን ትሩፋቶች ሁሉ በዚህች አጭር ፅሁፍ መቋጨት አይቻልም።

﴿ إِنَّ ٱلَّذِينَ يَتۡلُونَ كِتَٰبَ ٱللَّهِ وَأَقَامُواْ ٱلصَّلَوٰةَ وَأَنفَقُواْ مِمَّا رَزَقۡنَٰهُمۡ سِرّٗا وَعَلَانِيَةٗ يَرۡجُونَ تِجَٰرَةٗ لَّن تَبُورَ ٢٩ ﴾ فاطر: ٢٩

‹‹እነዚያ የአላህን መጽሐፍ የሚያነቡ ሶላትንም አስተካክለው ያደረሱ ከሰጠናቸውም ሲሳይ በምስጢርም ኾነ በግልጽ የለገሱ በፍጹም የማትከስርን ንግድ ተስፋ ያደርጋሉ›› አል-ፋጢር 29

ከዑመር ኢብኑል ኸጧብ በተወራውና ሙስሊም በዘገቡት ሀዲስ ነብዩ (ሠ.ዐ.ወ) ሀዲስ እንዲህ ይላሉ፡-

‹‹ إن الله تعالى يرفع بهذ الكلام أقواما ويضع به آخرين ›› رواه مسلم

‹‹አላህ በዚህ የአላህ ንግግር(ቁርዓን) ህዝቦችን ከፍ ያደርጋል! ሌሎችንም በዚሁ ቁርዓን ዝቅ ያደርጋል›› ሙስሊም ዘግበዉታል

‹‹ الذي يقرأ القرآن وهو ماهر به مع السفرة الكرام البررة ››رواه البخاري ومسلم

‹‹ቁርዓንን በአነባበብ ስልቱ ተክኖ የሚያነበዉ እርሱ መልካም እና አላህን ታዛዥ ከሆኑ መልዓክቶች ጋር ነዉ››

ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበዉታል

በሌላ ሀዲስ እንዲህ ብለዋል፡-

(اقرؤوا القرآن فإنّه يأتي يوم القيامة شفيعا لأصحابه) رواه مسلم

(ቁርአንን አንብቡ! ቁርአን በትንሳኤ እለት ለጓደኞቹ አማላጅ ሆኖ ይመጣል)

ሙስሊም ዘግበዉታል

እነዚህና ሌሎች ቁጥራቸዉ በዛ ያሉ ሀዲሶች የቁርአን ህዝቦችን ደረጃ ያሳያሉ

## ከቁርዓን ምንም አለመሃፈዝ

እንዲህ አይነቱን ሰዉ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በፈራረሰ ኦና ቤት መስለውታል፡፡ኢብኑ አባስ ከነብዩ ባስተላለፉት ሀዲስ እንዲህ ይላሉ፡፡

‹‹إن الذى ليس فى جوفه شئ من القرآن كلبيت الخرب›› رواه الترمذى

‹‹ ከቁርዓን ትንሽም ቢሆን በሆዱ የሌለው ሰው ምሳሌው እንደፈራረሰ አና ቤት ነው።›› ቲርሚዚይ ዘግበዉታል

## ቁርዓንን የሃፈዙ ሰዎች በዲኑ የተሰጣቸው ታላቅ ቦታ

ቁርዓንን የሀፈዙ ሰዎች ቁርአንን ለመጠበቅ አላህ ሰበብ ያደረጋቸው ሰዎች ናቸው።በዚህም ምክኒያት አላህ ደረጃቸዉን ከፍ አድርጎታል።

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በጣም ያከብሩዋቸውና ከሌሎች ያስቀድሟቸው ነበር። በኡሁድ ዘመቻ ላይ የተሰው ባልደረቦቻቸውን ሲቀብሩ ቁርዓን ብዙ የሃፈዙትን ያስቀድሙ ነበር።

ለኢማምነትም የሚመርጡት እና የሚያስቀድሙት በእድሜ እንኳ ትንሽ ቢሆን ቁርዓንን የተማረውን እና የሸመደደውን ነበር።

‹يؤمُّ القومَ أقرأُهُم لكتاب الله تعالى›› رواه مسلم

‹‹ሰዎችን በሰላት የሚመራዉ ከእነሱ መካከል ቁርአንን በደንብ የሚያነብ ሰዉ ነዉ›› ሙስሊም ዘግበዉታል

## ቁርዓን ስንቀራ የምንከተላቸው አደቦች (ስርዓቶች)

ምንዳችን ከፍ ይል ዘንድ ስርዓቶችን ጠብቀን መቅራት ይኖርብናል። ከነዚህም ስርዓቶች ውስጥ:-

ከመቅራት በፊት መፋቂያ መጠቀም ይወደዳል

ውዱዕ ማድረግ

የወር አበባ ላይ እና የወሊድ ደም ላይ ያሉ ሴቶች ሂፍዛቸዉ ን እንዳይረሱ ካላሰጋቸዉ ባያነቡ ይመረጥላቸዋል ።

ጀናብተኛ ሆኖ ማንበብ አይቻልም

እንደ መስጊድ ፅዳት ያለበት ቦታ ቢነበብ ይወደዳል

ወደ ቂብላ መዞር

ከማንበብ በፊት ተዐውዝ (አዑዙቢላሂ........) ማለት

በተደቡር እያስተነተኑ በሙሉ ስሜት ማንበብ አንቀፆችን በማስተንተን

ድምፅን ማሳመር

ከሱረቱ ተውባ በስተቀር በእያንዳንዱ ምዕራፍ መግቢያ ‹ቢስሚላሂ አረህማኒ አረሂም› በማለት መጀመር

እነዚህ ስርዓቶች የተከተለ ለቁርዓን ትልቅ ቦታ ሰጥቷል የነቢዩን ሱና ተከትሏል ደረጃው የላቀ መሆኑ አያጠራጥርም።

## ቁርዓን የሃፈዘ ሰዉ መገለጫ ባህሪያት

ቁርዓን የሃፈዘ ሰው ትልቅ ሃላፊነት አለበት ምክንያቱም የተሸከመው የአላህን ቃል ነውና። የሚከተሉትን ባህሪዎች የግሉ ማድረግ ይኖርበታል።

1ኛ. በሀፈዘዉ ቁርአን ሌሊት ሰላት ሊሰግድበት ይገባል

2ኛ. በፆም በኢባዳ መጠንከር አለበት

3ኛ. ቁርዓን በሚቀራበት ምላሱ አፀያፊ ነገር ሊናገርበት አይገባም

4ኛ. በመሃፈዙ መተናነስን አለበት እንጂ መኩራት የለበትም

5ኛ. ቁርአኑን የጥቅማ ጥቅም ማሳደጃ ሊያደርገዉ አይገባም

6ኛ በአጠቃላይ ቁርዓኑ በምላሱ ብቻ ሳይሆን በተግባሩ ላይ ሊታይ ይገባል

ለሌሎችም አርአያ መሆን ይኖርበታል፡፡ ‹የረሱል ባህሪ ቁርአን ነበር› ስትል ባለቤታቸዉ የምእመናን እናት ዓኢሻ ትናገራለች፡፡

## ከቁርዓን መራቅ

﴿ وَقَالَ © يَٰرَبِّ إِنَّ قَوۡمِي ٱتَّخَذُواْ هَٰذَا ٱلۡقُرۡءَانَ مَهۡجُورٗا ٣٠ ﴾ الفرقان: ٣٠

‹‹መልዕክተኛውም ጌታዬ ሆይ ሕዝቦቼ ይህንን ቁርዓን የተተወ ነገር አድርገው ያዙት አለ›› አል-ፉርቃን 30

ኢብኑል ቀይም ከቁርዓን መራቅ ብዙ አይነት እንደሆነ ጠቅሰዋል:: ከነዚህም ውስጥ :-

በቁርአን ከማመን መራቅ

በቁርአን አምኖ ግን በተግባሩ ላይ አለመገኘት

በቁርአን አለመዳኘት

ከማስተንተን እና ከማወቅ መራቅ

5. ከልብ በሽታዎች በቁርዓን ከመታከም መራቅ

እነዚህ ነገሮች በሙሉ ከቁርዓን ከማፈንገጥ (ሀጅር) ይመደባሉ፡፡ የማፈንገጥ ደረጃው ቢለያይም ግን ሁሉም ማፈንገጥ ናቸው ያፈነገጠ ዳግም አላህ የተጨናነቀ ኑሮን እንደሚሰጠዉና እና በዕለተ ትንሳዔ እውር አድርጐ እንደሚቀሰቅሰው ገልፆልናል፡፡

## ቁርአንን ማስተማር ምንዳው ምንድን ነው?

‹‹خيركم من تعلم القرآن وعلمه›› رواه البخاري

‹‹ከእናንተ በላጭ ቁርዓንን ተምሮ ያስተማረ ነው፡፡›› ቡኻሪ ዘግበዉታል

ቁርዓንን የሚያስቀራ ከሁሉም በላጭ ነው:: ቁርአንን የሚያስተምር ሰዉ እራሱን በኢኽላስ ሊያንፅ ይገባዋል፡፡ ለተማሪዉ የሚያዝን እና የሚያስብ፣ የሚያርም፣ መልካም ባህሪን የሚያወርስ ሊሆን ይገባል፡፡

## ቁርዓን መቅራት ድንጋጌው ምንድን ነው?

ቁርዓን መቅራት አራት አይነት ድንጋጌ አሉት፡፡ ግዴታ (ዋጂብ)፣ ክልክል(ሀራም)፣ የተጠላ(መክሩህ)፣ የተወደደ(መንዱብ)፡፡

ግዴታ የሚሆነው በሰላት ውሰጥ ሲሆን

2. የተወደደ የሚሆነው ደግሞ በማንኛውም ወቅት ስንቀራ ወይም በሰላት ላይ ከግዴታ ያለፈ ጨምረን ስንቀራ

3. የሚጠላው ኢማሙ ኹጥባ እያደረገ መቅራት ሰጋጆች እና የተኙ ሰዎች እያሉ ጨሆ መቅራት ወዘተ …

4. ክልክል የሚሆነው እንዲሰሙልኝ ብሎ መቅራት፣ ሽንት ቤት ውስጥ በቀብርና በመሳሰሉት ሸሪዓው ለኢባዳ ባልደነገጋቸው ቦታዎች መቅራት

## ሰለፎቻችን ቁርዓንን እንዴት ነበር የሚቀሩት?

ከፊሎቹ በየወሩ ሌሎቹ በየአስሩ ቀናት ሌሎቹም በየስምንት ወይም በየሰባት ቀናቱ ያከትሙ ነበር፡፡ ኡስማን ኢበኑ አፋን፣ተሚሙዳሪ፣ ሰዒድ ብኑ ጁበይር፣ ሙጃሂድ አና አል-ኢማሙ ሻፊዒይ በአንድ ቀንና ሌሊት ሙሉ ቁርዓን ያኸትሙ እንደነበር፤ አብዛኛዎቹ ሰለፎች ግን በየሰባት ሌሊት እንደሚያከትሙ ኢማሙ ነወዊ ገልፀዋል፡፡

## ቁርዓን መቅራት የሚወደድባቸው ጊዜያት አሉትን?

ኢማሙ ነወዊ እንደገለፁት ለመቅራት በላጩ ሁኔታ በሰላት ውስጥ ሲሆን በሌሊት የመጨረሻው ግማሽ ሌሊት ደግሞ ከመጀመሪያው የተሻለ ነው፡፡ በኢሻ እና በመግሪብ መካከልም መቅራት የተወደደ ነው፡፡ ሰላት በተከለከሉበት ወቅቶች ቢሆንም እንኳን፡፡ እንዲሁም በረመዷን ቁርዓን ማብዛት አለብን የቁርአን ወር ነዉና፡ በተለይም በመጨረሻዎቹ አስር ቀናቶች ከአስሮቹ ደግሞ በነጠላዎቹ (21፣ 23፣ 25……..) እንዲሁም በመጀመሪያዎቹ የዙልሂጃ አስር ቀናት በተለይም በዓረፋ ቀን ቁርአን መቅራትን ልናበዛ ይገባል፡፡፡፡ እነዚህ የተመረጡ ጊዜያት ናቸው፡፡

# አላህ ከቁርአን ህዝቦች ያድርገን

www.nesiha.com

www.biftuuislaamaa.com


**አል ፋሩቅ**

**የቁርአን ሒፍዝ ማዕከል**

**0912167857 / 0911347676**

**አዲስ አበባ**

**ኢትዮጵያ**